Mission Mobilization
ETHIOPIA



# “ክርስቶስን ከማሳፈር አንድ መቶ ጊዜ መሞት ይሻለኛል” --ጆን ካልቪን

## ጆን ካልቪን

ሐምሌ 10. 1505 - ግንቦት1564

በ ዶ/ር ግርማ በቀለ የተዘጋጀ

# ጆን ካልቪን

# ሐምሌ 10. 1505 - ግንቦት1564

# *** ከውስጥ ሞልቶ ለትውልድ የፈሰሰ የግል ተሐድሶ ***

“ክርስቶስን ካማሳፈር አንድ መቶ ጊዜ መሞት ይሻለኛል” --ጆን ካልቪን
በዓለምና በቤተ ክርስቲያን የሐድሶ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ካላቸው ታላላቅ መሪዎች መካከል፣ የፈረንሳዪ ጆን ካልቪን በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው። የሕግ፣ የነገር መለኮት፣ የፍልስፍና፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ በተለይም ጥንታዊ ግሪክ-ሮማ ሥልጣኔና ቋንቋዎች ጥናት ሊቅ ነበር። በታሪክ ውስጥ፣ በነገረ አስተምህሮ፣ በተለይም በድኅነት ዙሪያ፣ በቤተ ክርስቲያን ማንነትና ተልእኮ፣ በትምህርት፣ በዲሞክራሲ፣ በመንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መሠረታውያን ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል።

በ1533 አካባቢ አንድ ቀን የወንጌል ብርሃን በልቡ ላይ በራ - ሊቋቋመው ያልቻለው ትልቅ ብርሃን! ስለ ልቡ ለውጥ ሲናገር እንዲህ ብሎ ጾፏል፦
“እግዚአብሔር ልቤን በድንገት ለወጠው፤ ለእውነተኛውም የወንጌል ቃል አንበርከከው። በየዕለቱ እየጨመረ በሚሄድና የእግዚአብሔርን ቅድስና በሚጠማ መንፈሳዊ የውስጥ ግለት ነፍሴ ታሰረች።” (John Dillenberger, John Calvin, Selections from His Writings, 26)። ስለዚህ ወንጌል፣ “የንግግር ችሎታ፣ ወይም ከአፍ የማያልፍ ሕይወት የለሽ ደረቅ ታሪካዊ ዶክትሪን ሳይኾን ሥር-ነቀል በኾነ መልኩ የሕይወት መልእክት ነው። በአእምሮ የግል ጥረት፣ በረቀቀ አመክንዮና ሙት በኾነ ሃይማኖታዊ የፊደል ሽምደዳ ሊረዱት አይችሉም። የወንጌልን ጉልበት መረዳት የሚቻለው፣ ቅዱስ ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነፍስንና የውስጥ ልብን ሰርስሮ ሲገባ ብቻ ነው።" በማለት የወንጌልን ከሰው፣ በሰው ያልሆን ፈጹም መለኮታዊነት በሕይወት ምስክርነትና በአስተምህሮ ብቃት ሞግቷል። (Calvin, Golden Booklet of A True Christian Life, 20-21)።

የካልቪን ጥማት የእግዚአብሔር ክብር ነበር። ይኸው በግል ሕይወቱ ሞልቶ የፈሰሰው የእግዚአብሔር ክብር ነበር የቤተ ክርስቲያንና የዓለምን ታሪክ ዐቅጣጫ ያስቀየረው። በአደባባይና በግል ሕይወቱ መካከል ምንም የግብዝነት ክፍተት አልነበረም። የ24 ዓመት ወጣት በነበረበት ወቅት የፈርንሳይ ንጉሥ፣ ቀዳማዊ ፍራንሲስ፣ በወንጌል አማኞች ላይ ባስነሳው ሰደት ምክንያት ትውልድ አገሩን ጥሎ ወደ ጄኔቭ ተሰድዶ ነበር። ቀሪውንም ዘመኑን የጨረሰው እዚያው ጄኔቭ የቤተ ክርስቲያን ታማኝ መጋቢ በመሆን ነበር።
አራት መድብሎች ያሉት የካልቪን ኢንስቲቲዩት “Institutes of the Christian Religion” ያለፉት አምስት መቶ ዐመታት የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ቋሚ ቅርስ ነው።
(http://www.reformed.org/master/index.html?mainframe=/books/institutes/) ይህን የጻፈው የ27 ዓመት ወጣት በነበረበት ወቅት ነበር። ስለጻፈበትም ዋነኛ ምክንያት ሲናገር፦
“ክርስቶስን ለተራበውና ለተጠማው የአገሬ ሕዝብ ካለኝ ሽክም የመነጨ ነው . . . በባዚል (ስዊዘርላንድ) ነፍሴን ለማዳን በተደበቅሁበት ሁለት ዓመታት፣ እንደ እኔ ከሰደት የማምለጥ ዕድል ያላገኙ የወንጌል አማኝ ወዳጆቼ፣ በሕይወት እያሉ በማገዶ እሳት ጋይተው ስለ ክርሰቶስና ስለበራላቸው እውነት ሰማዕት ሆነዋል። ታዲያ ይኽን እያወቅሁ ዝም ብል ከዳተኛ፣ ሰማዕትነታቸውንም አቅላይ ያደርገኛል። የሞቱለትን ጌታና የወንጌሉን መልእክት በፍጹም ንጽሕና ለትውልድ ማትረፈ ትንሹ ዕዳዬ ነው። ፈጽሞውኑ ዝናንና ክብርን ፍለጋ አይደለም።”

እኛስ፣ ምን ሠርተን ይኾን የምናልፈው?
የካልቪን የውስጥ ጩኸት፣ በሙት ሃይማኖትኘነትና ከቃሉ ጋር በሚጋጭ ትውፊት ከትውልዱ የተሰወረውን የክርስቶስን ሥራና ክብር መግለጥ ነበር። በክርሰቶስ የተገኘው የማይቀነሰበት፣ የማይጨመርበትና ብቁ የኾነ ብቸኛ የድኅነት ሙሉ ሥራ የካልቪን መካከለኛ አስተምህሮ ነበር። ለካልቪን ጌታ ኢየሱስ ክርሰቶስ "ማንም ሊሸፍነው የማይገባ የእግዚአብሔር መካከለኛ ግርማ" ነው። የፓፓው ሥልጣን የማይገሠሥና ከቃሉ በላይ ከፍ ባለበት ዘመን ነበር ካልቪን በነፍሱ በመወራረድ፣ “ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ ቃሉ ተወለደች እንጂ፣ ቃሉ ከቤተ ክርስቲያን አልተወለደም” በማለት የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን ፍጹማዊ የራስ ግንዛቤ ፊት ለፊት ተቃውሞ ነበር። (Institutes, 1.7.2)

# ጆን ካልቪን
# ሐምሌ 10. 1505 - ግንቦት1564
# *** ከውስጥ ሞልቶ ለትውልድ የፈሰሰ የግል ተሐድሶ ***

በዚህ አቋሙ ካልቪን በብዙ መከራ ውስጥ ዐልፏል። መዝሙር 124፣ በተለይም፣ ቁጥር ስምንት፣ "ረድኤታችን ስማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።" የልቡ ጥቅስ ነበረች። ባለቤቱ ኢደሌት (Idelette)፣ ቀደም ሲል ታማኝ የወንጌል አገልጋይ ባሏ የሞተባትና የኹለት ልጆች እናት ነበረች። ከካልቪን የወለደችው የመጀመሪያ ልጃቸው የኹለት ሳምንት ሕፃን ሳለ ነበር ያረፈው። ስለ ልብ ስብራቱም እንዲህ በሎ ጽፏል፦
“ጌታ በሐዘን ጅራፍ ልቤን ያቆሰለው እስኪመስለኝ ድረስ የልጄ ሞት አጥንቴ ውስጥ ዘልቆ ገብቷል። ይኹን እንጂ እርሱ ራሱ ሰማያዊ አባት ስለሆነ ልጅ ማጣት ምን ማለት እንደሆነ ይገባዋል፤ የእርሱም ፈቃድ ፍጹም፣ ለልጃንም የተሻለውን ያውቃል በማለት በፍጹም ሉዓላዊነቱ ተጽናናሁ” (T. H. L. Parker, Portrait of Calvin, 71)።

በተከታታይ የወለዷቸው ልጆች፣ በመጨረሻም ኢደሌት ራሷ በወረርሽኝ ወይንም በሳንባ ነቀርሳ ምክንያት በተጋቡ በዘጠነኛው ዐመት ላይ ሞታበታለች። በዚህ ሁሉ የልብ ስብራት ውስጥ፣ ልቡን በእግዚአብሔር አምላኩ ያበረታ የተሐድሶ መሪ ነበር። በትጉህ ነበር። በኹለት ሳምንት ውስጥ 10 ጊዜ (እሁድ ቀን ብቻ ኹለት ጊዜ) እንዲሁም በሳምንት ሦስት ቀን ያስተምር ነበር። ከዮሐንስ ራእይ በስተቀር በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ በአምስቱም ኦሪቶች፣ በመዝሙረ ዳዊት፣ በኢሳይያስና መጽሐፈ ኢያሱ ላይ ማብራሪያ ጽፏል። ይህን ሁሉ ይባትል የነበረው በጄኔቭ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን መጋቢነቱ በተጨማሪ ነበር። በየቤቱ የታመሙትን፣ የተቸገሩትን፣ የተጨነቁትን፣ ወላጅ አልባዎችንና ችግረኛ ባልቴቶችን በታማኝነት ይጐበኝ ነበር። መጋቢነት በተግባር ማለት ይኸው አይደል?

በተገኘበት ማንም ሰው እንዲገድለው ቀዳማዊ ፍራንሲስ ያወጀበት የሞት ዐዋጅ ድባብ በላዪ ላይ እያንዣበበ፣ የተመጣጠነ ምግብ ዕጥረት፣ በኩላሊት፣ በጨጓራ ቍስል፣ በሆድ ድርቀትና በተመሳሳይ የጤና መታወክና እንቅልፍ በማጣት ይሰቃይ ነበር። መከራን በትዕግሥት የተቀበለ - ኑሮ ሳይመቸው ያለፈ ታማኝ የወንጌል ባለዐደራ! እንደ ጳውሎስ፣ “በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን ነበር። በርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደብን ይሰማን ነበር፤” (2ቆር 1፡ 8-9) ያለባቸው ብዙ ሞትን የተመኘባቸው የጨለማ ወቅቶች አሳልፏል። ይሁን እንጂ፣ “ክርስቶስን ካማሳፈር አንድ መቶ ጊዜ መሞት ይሻለኛል” ነበር የውስጥ ጥንካሬው! (Henry F. Henderson, Calvin in His Letters, 77.)። እናም ብድራቱን ትኩር አድርጎ ዘላለምን በማሰብ ያገለገለ ባሪያ!

ረድኤታችን የሆንከው ጌታችን ሆይ፣ “ክብርህን ተጠሚዎች፣ ለራሳቸው ፈቃድ የሞቱ ባሪያዎችና ታማኝ የወንጌል ዐደራ ጠባቂዎች አድርገን። በመከራችን ደግሞ ጸጋህን አብዛልን”። አሜን!

በዶ/ር ግርማ በቀለ የተዘጋጀ